www.ginbot7.org

# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7፣ የፍትሕ፣የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

ሐምሌ 3 2000 ዓም ቁጥር 8

---

## ርእሰ አንቀጽ;  የነብርን ጭራን አይይዙም ፤ ከያዙም ...

«መድረክ ለዴሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ» (መዴምኢ) የተሰኘ ስብስብ የመመሥረቱን ዜና በአንክሮ ተመልክተነዋል :: በእስር የተንገላቱ ዜጎች ፤ በግንቦት 97 ምርጫ የህዝብን ቀልብ በከፊል የሳቡ ድርጅቶች ፤ በጥቅሉ ደግሞ በህጋዊ ተቀናቃኝነት የተመዘገቡ ፓርቲች ፤ በዋና መልኩ በብሄረሰብ አደረጃጀት የሚያምኑ ስብስቦች ፤ በአመዛኙ በ1983ቱ የሽግግር መንግስት በባለሥልጣንነት ያገለገሉ የሃገር መሪች የተካተቱበት መድረክ በመሆኑ ልዩ ትኩረት ሰጥተነዋል :: ከሽግግር መንግስቱ ጅማሮ እስካሁን ለ17 አመታት በምድረ-ኢትዮጵያ ለሰፈነው ብካይ በቂ ምላሽ ይሆናል ብለን ባናምንም እንኳ ፤ በግንቦት 97 ህብረ-ብሄር የፖለቲካ ሃይሎች በምርጫው ሲያሸንፉ ፤ «በስንት መስዋአትነት ያመጣኸውን ህገ-መንግስተዊ ሥርአት የሚቀለብሱ ትምክህተኞች ተመልሰው መጡብህ» በሚል ዘረኛ ቅስቀሳ የመከላከያና የፀጥታ ሀይሉን በማስደንበር በከተሞች ብቻ ከ200 ለማያንሱ ዜጎች ፍጅት እንዲተባበሩት ማድረግ በመቻሉ ፤ አሁን የተቋቋመው የ«ምክክር መድረክ» በተመሳሳይ ክስ ሊከሰስ የማይመች በመሆኑ ፤ ሥርአቱ ከገባበት ድቀትና የመከላከያ ሃይሉም አካባቢ ከሚታየው መፍረክረክና መረበሽ አኳያ ፤ ሃገሪቱ ወዳልታሰበ ቀውስ ውስጥ እንዳትገባና ፤ መልክ ያለው ሽግግር ለማድረግ የሚረዳ ፤ የፀጥታና የመከላከያ ሃይሉ ለአመታት ከተሰገሰገበት ጠባብ ብሄርተኛ አመለካከት አንፃር ፤ በተሻለ ሊያምነው የሚችል መድረክ ሊሆን ይችላል የሚል በጎ ግምት አለን ::

ይህ በጎ ግምታችን ግን ፤ ከውስጣችን የሚመነጭ የተስፋ ድልድይ እንጂ ፤ የ«ምክክር መድረኩ»ን የመሠረቱት መሪች በ1983ቱ የሽግግር መንግስት ወቅት ያሳዩትን ፀረ-ኢትዮጵያዊነት ዝንባሌና አድራጎት በመርሳት አይደለም :: እኛም ይቅር ለማለት ባለን ሆደሰፊነት ፤እነርሱም ከሥልጣን በተገለሉባቸው አመታት በህዝባዊ መድረኮች ካሰሙዋቸው የፀፀት አነጋገሮች በመነሳት እንጂ :: ያወጡት መግለጫ ግልፅ እንደሚያደርገው ከሽግግር መንግስቱ እስከዛሬ ባለፉት 17 አመታት የተፈጠረውን የመለስ ክህደት እመቃና የኢትዮጵያችን ሉአላዊነት መደፈር እንዳስቆጫቸው ግልፅ ነው :: በክልል ኬላ የተሸማቀቀውን የህዝባችንን የመሥራትና የመበልፀግ መብትም በሚመለከት ያቀረቡት መፍትሄ ተገቢ ነው :: መሠረታዊ የፖለቲካ ዴሞክራሲና የነፃነት መብቶች እንዲከበሩ ያደረጉት ጥሪ የዘመኑ :: ሆኖም ሥርአቱ በሠላም እንዲለወጥ በግንቦት 1997 ሃገሬው ከአድማስ እስከ አድማስ ያደረገውን የምርጫ ንቅናቄ የሚገባውን ታሪካዊ ቦታ መግለጫው ያለማካተቱ ግን ጉልህ ቀዳዳ ሆኖ ታይቶናል :: ስለ ግንቦት የህዝባችን ዴሞክራሲያዊ ጥማት አንዳችም ቃል አለመተንፈስና ሆኖም ለ2002 ምርጫ አቅምን ለማሰባሰብ ማለም ፤ አንድም የመለስ ሥርአት በህጋዊ መንገድ በህዝብ ምርጫ ሥልጣን ላይ እንደሚገኝ ማስመሰል ፤ አለያም ለግንቦት ታሪካዊ ክንዋኔ የሚገባውን ክብደት አለመስጠት እንዳይሆን እንፈራለን :: በቀጣዮቹ ሉሎች «የምክክሩ» መግለጫች ዕርምቱን ለማየት ጉጉታችን ነው ::

የ«ምክክር መድረኩ» በመከላከያና የፀጥታ ሃይሎች ተአማኒ ለመሆን ካለው አቅሙም በመነጨ በሥርአቱ በጭካኔ የመወገዱም አደጋ ወለል ብሎ ይታየናል :: ምንሊክ ቤተመንግስት ውስጥ ሽብሩ እየተጧጧፈ መሆኑም ጭምጭምታው መሰማት ጀምሯል :: የ«ምክክር መድረኩ» ይፋ በተደረገ ማግስት የመለስ ማስታወቂያ ሚኒስትር ተሯሩጦ «ለግጭቶች መፈጠር መንስኤ የሆኑትን ምክንያቶች በመፍጠር ፤ መልሶ መንግስትን መክሰስ አይገባም/አይቻልም» የሚል መግለጫ ማውጣቱ የሚጠቁመውም ፤ «በትምክህተኞች መጡብህ» ሊያስደነብረው የማይችለውን የፀጥታና መከላከያ ሃይል፤ በሌሎች ክሶች ለማነሳሳት አያደባ መሆኑን ነው :: በቅንጅቱ ላይ ከደረሰው ዕመቃና ዕልቂት በበለጠ በ«ምክክር መድረኩ» መሪችና አባላት ላይ ሊደርስ እንደሚችል መገመት ጠንቋይ መቀለብን አይጠይቅም :: መለስ ፤ ዕንቅልፍ የሚያጣለትን ሥልጣን የበለጠ

ሊነጥቁኝ ይችላሉ ብሎ ስለሚባንን ፡፡ ከግንቦት 97 ምርጫ ሁሉም መማር ያለበት ትምህርት ይሄው ነውና ፡፡ ለ«ምክክር መድረክ» መሪችም ያለን ምክር «የነብርን ጭራ አይይዙም .... » ነው ፡፡ በግንቦት የህዝብ ድምፅ ክፉኛ የቆሰለ ነብር በመሆኑም «የቆሰለ ነብርን ጭራ...» ማለቱም የጉዳዩን ክብደት ያሳያል እንላለን ፡፡ ለማንኛ ውም «የግንቦት ሰባት ንቅናቄ» ማንኛውንም የኢትዮጵያን የዴሞክራሲ ተስፋ በአንዲት ጋትም ቢሆን ወደግቡ ፊቅ የሚያደርግን የዜጎች ሙከራ ሁሉ በአድናቆት የሚቀበለው ስለሆነ ፤ የ«ምክክር መድረኩ»ንም መቋቋም በተመሳሳይ ስሜት የተቀበለው መሆኑንም መግለፅ ይወዳል ፡፡